# ሰለት ላይ

ካዱንያ ሳይጠሩ
ደረሱ ከበሩ
ገቡ ከመስጊዱ
ሀረሙ ሊሰግዱ
በአይንዎ ፈለጉ
ከበር እስከጥጉ
ኮት አስተካከሉ
ሱሪ ተቀለሉ
ሰአትዎንም አዩ
ሰንት እንደሆነ ለዩ
ፀግርዎን አከኩ
ኪስዎትን ነካኩ
ሞባይል ዘነጉ
አነሱና ዘጉ
ኮፍያ አወለቁ
ቀበቶ አጠበቁ
ጉንጩውን ደባበሱ
ፊትዎንም አበሱ
አይናርዎን ጠረጉ
ፂምዎን ፈገፈጉ
ንፍጥዎን ተናፈጡ
ጥፍርዎን ቆረጡ
በሃሳብ ይነጉዳሉ
በኩም የሄዳሉ
አንዴ ፈገግ ሲሉ
ደግሞም ኮስተር ሲሉ
በሃሳብ ፈረሱ
ከካፌው ደረሱ
ከአፍታው ላሱ
ሂሳብ አስታወሱ

ደመሩ ቀነሱ
ሪከርድ ሊሰብሩ
ማርሽ ቀያየሩ
ሱብሂን በዝረራ
አስርን በፋከራ
በበርጫ ውጠራ
መግሪብን በበቃኝ
ኢሻን በአፋጣኝ
ጣሉና ደነፉ
ጉራዎንም ነፉ
የአይንዎ ማረፍያ
የድካምዎ መርግያ
የመንፈስ ማደሻ
የሃሳብ ማስረሻ
ሰላትዎ ናትና
አያሳጧት ጤና
አልሰገዱምና
ይስገዱ እንደገና
ባይሆን እንዲህ ያድርጉ
እንዳይዘናጉ
ለሰላት ሲቀርቡ
ሃሰብ ያሰባስቡ
በሃሳቦ ላይ ይንገሱ
ሶላቶን አይርሱ
(በሐምዱ ኢድሪስ)